# የሚጠረጠር በደል እና የቸልተኝነት ሪፖርት

የሠራተኞች ጉዳይ ዋና ኃላፊ ጽ/ቤት
የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
Office of the Chief of Staff
(MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS)
Rockville ፣ Maryland 20850

የ MCPS ቅጽ 335-44
ጁላይ 2019

*መመሪያዎች፡-* የቃል ሪፖርት (በተለምዶ የልጅ (ጥቃት/በደል) መከላከያ አገልግሎቶች/ Child Protective Services/ (CPS) ተብሎ ለሚታወቀው) የልጆች ተራድኦ አገለግሎቶች /Child Welfare Services, Montgomery County የጤና እና የሰው ሃይል አገልግሎቶች መምሪያ (DHHS) በ240-777-4417 በመደወል ሪፖርት መደረግ አለበት። ለጥቃት/ለጉዳት የተጋለጡ/ አቅመ ደካማ ትልቅ/አዋቂ ሰዎችን በተመለከተ፣ ለለአዋቂ/ትልቅ ሰው (ጥቃት/በደል) መከላከያ አገልግሎቶች/Adult Protective Services (APS) በ240-777-3000 ላይ ይደውሉ። ይህ የአስቸኳይ/ድንገተኛ አደጋ ጉዳይ ከሆነ፣ በአስቸኳይ ለ Montgomery County ፖሊስ መምሪያ (MCPD)፣ በ 911 ወይም በ 301-279-8000 ላይ ይደውሉ። ይህን የጽሁፍ ሪፖርት ሞልተው በ 48 ሰዓታት ውስጥ ያቅርቡ ።

የበደል እና ቸል መባል (ተገቢ እንክብካቤን ያለማግኘት) ሁኔታን ሪፖርት በማድረግ እና ባለማድረግ ላይ ጥርጣሬ የሚኖር ከሆነ ፣ ሁልጊዜ ቢሳሳቱም እንኳ ሪፖርት ማድረጉን ይምረጡ።

የ MCPS ሠራተኞች፣ የሥራ ተቋራጮች፣ ወይም የበጎ ፈቃድ አገልጋዮች ማንኛውንም ተጠርጣሪ ተጎጂ፣ ምስክር፣ ወይም ጥቃት አድራሽ መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ ወይም ከእነርሱ የጽሁፍ መግለጫዎችን መሰብሰብ አይኖርባቸውም።

## ክፍል I — የቃል እና የጽሁፍ ሪፖርት በሚያደርገው/በምታደርገው ግለሰብ የሚሞላ

ሥም________________________________ የሥራ ኃላፊነት/ሥልጣን ________________

የት/ቤት ሥም ________________________________ ኢ-ሜይል፡- ________________

የት/ቤት አድራሻ ________________________________ የት/ቤት ስልክ_____-_____-_______

መንገድ ከተማ ስቴት ዚፕ ኮድ

## ክፍል II—ስለ ልጅ ወይም አቅመ ደካማ ትልቅ/አዋቂ ሰው መረጃ (በሪፖርት አድራጊው/ዋ የሚታወቅ/የምትታወቅ ከሆነ/ች)

በሚያሰጋዎት ጉዳዮች ላይ ምልክት ያድርጉ:- ❏ የተፈጸመ በደል (ለይተው ይግለጹ) ❏ የአካል ጥቃት እና/ወይም ❏ ወሲባዊ ጥቃት) ❏ ችላ የተባለ/ች ❏ የአ እምሮ መጎዳት

ልጁ/ልጅቱ የተወለደ(ች)በት ቀን ____/____/_____ ዕድሜ____

የወሲባዊ ጥቃት ከተጠረጠረ፣ ርእሰ መምህር/ተቆጣጣሪ ለልዩ ተጎጅዎች/ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል (Special Victims Investigations Division)፣ MCPD፣ ወዲያውኑ በ 240-773-5400 ላይ መደወል አለባቸው ።

የልጁ/ጅቷ ሥም ________________________________ ጾታ፡- ❏ ሴት ❏ ወንድ ዘር______________ ክፍል________

አድራሻ ________________________________________________

ወንድም እህቶች (ከታወቁ)

| ሥም | እድሜ | የሚማርበት/የምትማርበት ት/ቤት | ሥም | እድሜ | የሚማርበት/የምትማርበት ት/ቤት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| | | | | | |

## ክፍል III— ለልጁ/ጅቷ ወይም ለአቅመ ደካማው/ዋ ትልቅ ሰው እንክብካቤ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት/ባት ግለሰብ (በሪፖርት አድራጊው/ዋ የሚታወቅ/የምትታወቅ ከሆነ)

በዚህ አድራሻ ነዋሪ የሆነ ለልጁ/ልጅቱ ኃላፊነት ያለው አዋቂ ሰው፡ _____

ዝምድና/ግንኙነት ❏ እናት ❏ አባት ❏ ሞግዚት

❏ ሌላ ________________________________

ስልክ #1 _____-_____-______ስልክ #2 _____-_____-______

ስልክ #3 _____-_____-______

በዚህ አድራሻ ነዋሪ የሆነ ለልጁ/ልጅቱ ኃላፊነት ያለው አዋቂ ሰው፡ _____

ዝምድና/ግንኙነት ❏ እናት ❏ አባት ❏ ሞግዚት

❏ ሌላ ________________________________

ስልክ #1 _____-_____-______ ስልክ #2 _____-_____-______

ስልክ #3 _____-_____-______

## ክፍል IV—የጉዳቱ ወይም የሚያሳስበው ሁኔታ ባህሪ (አስፈላጊ:- የተጠረጠረ የበደል/ጥቃት ወይም ችላ የተባለ (ተገቢውን እንክብካቤ ያለማግኘት) ጉዳይ ትክክለኝነት ለመወሰን ምርመራ ማድረግ የማንም የ MCPS ሠራተኛ፣ የስራ ተቋራጭ፣ ወይም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጭ ኃላፊነት አይደለም)። የ MCPS ቅጽ 336-01ን ይጠቀሙ፡- ለ MCPS ቅጾች እንደተጨማሪ ሆኖ የሚያገለግል፣ አስፈላጊ ከሆነ። ለተጨማሪ መረጃ፣ የቦርድ ፖሊሲን JHC እና የ MCPS ን መመሪያ JHC-RA ያጣቅሱ/ይመልከቱ።

ልጁ/ቷ ወይም ለጥቃት የተጋለጠው/ችው ትልቅ/አዋቂ ሰው የበደል እና ቸል የመባል ተጠቂ/ተጎጂ ሊሆን ይችላል ወደሚለው ጥርጣሬ የመራዎትን ሁኔታ እንዴት እንዳወቁ ይግለጡ። ስለ አሁኑ ጉዳቶች አግባብ ከሆነ፣ መረጃ ያካቱ።

በዚህ/ች ልጅ ወይም አቅመ ደካማ ትልቅ/አዋቂ ሰው ወይም በሌሎች በዚህ ቤተሰብ ሁኔታ ውስጥ በሚገኙ፣ስለደረሱ/ስለነበሩ ቀደም ያሉ የ CPS ወይም የ APS ተሳትፎን ጨምሮ፣ የበደል/የጥቃት ወይም ቸል የመባል ጉዳቶች ወይም ሁኔታዎች መረጃ ያቅርቡ:-

## ክፍል V— እታች የሚጠየቀውን መረጃ ይሙሉ

የቃል ሪፖርቱ የተደረገበት ቀን ____/____/_____ የቃል ሪፖርቱ የተደረገበት ሰአት ___:___ a.m./p.m.

የቃል ሪፖርት የተደረገለት/ላት የ CPS ወይም APS ሠራተኞች አባል ሥም። (እባክዎን ይጻፉ) ________________

ርእሰ መምህሩ/ሯ/ ተቆጣጣሪው/ዋ እንዲያውቁት የተደረገበት ቀን እና ሰአት። ቀን ____/____/_____ ሰአት ___:___ a.m./p.m.

ይህ ቅጽ ለ CPS ወይም ለ APS የተላከበት ቀን ____/____/_____ የሪፖርት አድራጊው ሰው ፊርማ ________________

**DISTRIBUTION:**
**COPY 1: CPS, DHHS**, 1301 Piccard Drive, Rockville, MD 20850, Phone: 240-777-4417; or **APS, DHHS**, 401 Hungerford Drive, 3rd Floor, Rockville, MD 20850, Phone: 240-777-3000
**COPY 2: MCPS Systemwide Child Abuse Contact,** Office of the Chief of Staff, CESC, Room 162, Phone: 240-740-3215
**COPY 3: Office of the State's Attorney for Montgomery County**, County Office Building, 50 Maryland Avenue, 5th Floor, Rockville, MD 20850;
**COPY 4: Special Victims Investigations Division**, Montgomery County Police Department, 7300 Calhoun Place, Suite 300, Rockville, MD 20855, Phone: 240-773-5400.

ምስጢራዊ መረጃ የያዙ የበደል እና ችላ የመባል ሪፖርቶች ካልታዘዘ/ካልተፈቀደ በቀር ሊሰራጩ፣ ሊበተኑ፣ ወይም ሊገለበጡ/ኮፒ ሊደረጉ አይችሉም። መግለጽ/ጥ፣ መገልበጥ/ኮፒ ማድረግ፣ ማሰራጨት፣ ወይም በዚህ መረጃ ይዘቶች ላይ መሰረት በማድረግ ማናቸውንም እርምጃ መውሰድ በጥብቅ የተከለከለ ነው ።

የበደል እና ችላ መባል (ተገቢ እንክብካቤን ያለማግኘት) ሁኔታን ሪፖርት በማድረግ እና ባለማድረግ ላይ ጥርጣሪ የሚኖር ከሆነ፣ ሁልጊዜ ቢሳሳቱም እንኳ ሪፖርት ማድረጉን ይምረጡ ።

## ትርጉሞች

በደል (ጥቃት) ማለት፡-

1. ማንኛውም የአካል መጎዳት በግልጽ የማይታይም ቢሆን፣ አእምሮው የተጎዳ ልጅ ወይም ለጥቃት የተጋለጠ አዋቂ ሰው በመደበኛነት ወይም በጊዜያዊነት ጠባቂ/ተንከባካቢ ወይም ክትትል በሚያደርግ ሰው አማካይነት የተፈጸመ፣ የልጁ/የልጅቱን ወይም ለጥቃት የተጋለጠ አዋቂ ሰውን ጤንነት ወይም ደህንነት ለጉዳት በሚዳረግ/በሚያጋልጥ ሁኔታ ወይም የተጎዳ/ች መሆኑን የሚያመለክት ከሆነ።
2. ማንኛውም የወሲባዊ ድርጊት ወይም ድርጊቶች (ለአካላዊ ጉዳቶች ይዳርጉ ወይም አይዳርጉ) እንደ የልጆች ወሲባዊ በደል/ጥቃት ወይም ብዝበዛ፣ በዘመዳሞቾች መካከል የሚደረግ የወሲባዊ ግኑኝነት፣ መድፈርን፣ በማንኛውም ደረጃ ወሲባዊ ጥቃት መፈጸምን፣ ግብረሶዶማዊ ወይም ተፈጥሯዊ ያልሆነ ወይም ያልተለመደ እና ተቀባይነት የሌለው የወሲብ ልምምዶችን ያካተተ በልጅ ወይም በአቅመ ደካማ ትልቅ ሰው ላይ፣ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ የማሳደግ ወይም ልጁ/ጅቷን ወይም አቅመ ደካማው/ዋን ሰው የመንከባከብ ወይም የመቆጣጠር ኃላፊነት ባለበ/ባት በማንኛውም ሰው የደረሰ/የተፈጸመ። ፆታዊ ትንኮሳ ወይም ማጎሳቆል የሚያካትተው፣ በዚህ አይወሰንም፣ ትንሽ ልጅ ወይም ደካማ አዋቂ ሰው ራቁት ሰውነት መነካካት፣ ብልት በማሳየት ለግብረስጋ ማነሣሣት፣ ሩካቤ ስጋ ማድረግ/ማስገባት፣ መሳም፣ መደባበስ/ማሻሸት፣ በማንኛውም ደረጃ ጾታዊ ወንጀል መፈጸም፣ አስገድዶ መድፈር፣ ወራዳነት፣ ሽርሙጥና፣ በህገወጥነት ሰዎችን ማዘዋወር፣ ወይም መፍቀድ/ፈቃድ መስጠት፣ ማደፋፈር፣ ወይም ልጅ ወይም ደካማ አዋቂ ሰው ወሲብ ቀስቃሽ ምስል/ፅሁፍ ማሳየት፣ ፎተግራፍ ማንሣት፣ ፊልም መቅረጽ፣ ወይም ስለ ትንሽ ልጅ ወይም ደካማ ትልቅ ሰው በህግ የተከለከለ የጽሑፍ/ሥዕላዊ ገለጻ፣ ወይም ትንሽ ልጅ ወይም አቅመደካማ ትልቅ ሰውን አስገድዶ የመድፈር ወንጀል በመሥራት የተመዘገበ ሰው ባለበት ወይም ሁልጊዜ በሚገኝበት አካባቢ እንዲቆዩ/እንዲኖሩ መፍቀድ።

ልጅ፡- የሚያመላክተው ማንኛውንም የ MCPS ተማሪ፣ የተማሪው/ዋ እድሜ ምንም ይሁን ምን፣ እና ሌላ እድሜው/ዋ ከ18 አመት በታች የሆነ/ች ማንኛው/ዋንም ሰው ነው። ምንም እንኳን የ Maryland ህግ ከ18 አመት በላይ የሆነ/ችን ተማሪ በደል ወይም ቸል መባልን በአጠቃላይ እንደ ወንጀል ባይወስደውም፣ MCPS ይህን የመሰለ ሁኔታ ከ18 አመት በታች በሆነ/ች ልጅ ላይ ደርሷል ተብሎ የተጠረጠረን በደል እና ቸል የመባል ሁኔታ ሪፖርት የሚደረግበትን ተመሳሳይ አካሄዶች በመጠቀም እንዲመለከት/ሪፖርት እንዲደረግ ይጠብቃል

የአእምሮ ጉዳት፡- ማለት ለልጁ/ጅቷ ወይም አቅመ ደካማው/ዋን ትልቅ ሰው ዘላቂ ወይም ጊዜያዊ የማሳደግ/የመጠበቅ ወይም ልጁ/ጅቷን ወይም አቅመ ደካማው/ዋን ትልቅ ሰው ለመንከባከብ ወይም ለመቆጣጠር ኃላፊነት ባለበ/ባት በማንኛውም ሰው ድርጊት ምክንያት ሊታይ የሚችል፣ የሚለይ፣ እና የልጁ/ጅቷ ወይም የአቅመ ደካማው/ዋ ትልቅ ሰው አእምሮ ወይም የስነ-ልቦና ችሎታ በአግባቡ ለመስራት በጉልህ መጎዳት/መጉደል ነው።

ችላ ማለት፡- ልጅ ወይም ደካማ አዋቂ ሰው ብቻው(ዋ)ን መተው ወይም ሌላ ተገቢ እንክብካቤ ያለማድረግ፣ ወይም ትኩረት አለመስጠት፣ ወይም ተገቢ ያልሆነ አያያዝ ወይም ትኩረት መንፈግ፣ ልጅ ወይም ደካማ ለጉዳት የተጋለጠ አዋቂ ሰው በማንኛውም ወላጅ፣ ጠባቂ፣ ቤተሰብ ወይም የቤተሰብ አባል፣ ጎረቤት፣ የ MCPS ሠራተኛ፣ በጎ ፈቃደኛ፣ ወይም ኮንትራክተር፣ ኃላፊነትው ያለው/ያላት ሰው፣ ወይም ማንኛውም በጊዜያዊነት ወይም በመደበኛነት የሚጠብቅ ሰው፣ ስለህፃኑ ወይም ደካማ ጎልማሳ ሰው ያሉበት አስጊ ሁኔታ የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለበት ሰው የሚከተሉትን አመላካች የሆነ —

ሀ) የልጅ ወይም አቅመ ደካማ ትልቅ/አዋቂ ሰው ጤና ወይም ደህንነት ሲጎዳ ወይም በሚታይ/ጉልህ የመጎዳት አደጋ ላይ ሲሆን፣ ወይም
ለ) በልጅ ወይም አቅመ ደካማ አዋቂ/ትልቅ ሰው ላይ የአእምሮ ጉዳት ሲደርስ ወይም ሊደርስ ያለ የአእምሮ ጉዳት ጉልህ አደጋ።

ለችግር የተጋለጠ ጎልማሳ ሰው ማለት፡- 18 ዓመት እድሜ ወይም የበለጠ ሪፖርት በሚያደርገው/በምታደርገው ግለሰብ እይታ የተጎሳቀለ ወይም ችላ የተባለው የእለት ተእለት ፍላጎትን ለመንከባከብ አካላዊ ወይም የአእምሮ ብቃት እንደሌለው ሲታመን ነው።

## ሪፖርት ማቅረቢያ መስፈርቶች

1. ሁሉም የ MCPS ሠራተኞች፣ የሥራ ተቋራጮች፣ እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጭዎች ማንኛውንም የሚጠረጠር የልጅ በደል ወይም ችላ መባል አጋጣሚ በግል እና በቀጥታ እንዲያመለክቱ የ Montgomery County የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ነው:-
   - ተጠቂ ነው/ናት ተብሎ/ላ የሚጠረጠረው/የምትጠረጠረው በአመልካቹ/ቿ በግለሰብ ደረጃ ይታወቅም/ትታወቅም አይታወቅም/አትታወቅም።
   - ድሮ በደል እንደደረሰ ለማመን ምክንያት በሚኖርበት በማንኛውም ጊዜ፣ ምንም እንኳን አጋጣሚው ሲታወቅ/ሲገለጥ ተጠርጣሪው/ዋ ተጎጂ ትልቅ ሰው ቢሆንም/ብትሆንም።
   - ልጁ/ልጂቱ ወይም አቅመ ደካማው/ዋ አዋቂ የትም ይኑር/ትኑር እናም የተጠረጠረው በደል ወይም ችላ መባል/ተገቢውን እንክብካቤ ያለማግኘት ተፈፀመበት የተባለው ስፍራ የትም ይሁን የት።
2. የተጠረጠረን በደል ወይም ችላ መባል ጉዳይ አሳማኝነቱን ለመወሰን መመርመር የማንም የ MCPS ሠራተኛ፣ የስራ ተቋራጭ፣ ወይም የበጎ ፈቃድ አገልጋይ ኃላፊነት አይደለም።
3. ስለተጠረጠረ የልጅ በደል እና/ወይም ችላ መባል (ተገቢውን እንክብካቤ አለማግኘት) የሚቀርብ የቃል ሪፖርት ወዲያውኑ መቅረብ አለበት፡-

የልጅ መበደልን፣ ቸል መባልን (ተገቢውን እንክብካቤ አለማግኘት)፣ እና የአእምሮ ጉዳት ሪፖርት ለማድረግ የሚከተለውን ቁጥር ይደውሉ
፡- 240-777-4417
የልጅ መከላከያ አገልግሎቶች (Child Protective Services)፣ የጤና እና የሰው ኃይል አገልግሎቶች መምሪያ (24 ሰአት)

ስለአቅመ ደካማ ትልቅ/አዋቂ ሰው በደል ወይም ቸል መባል (ተገቢውን እንክብካቤ አለማግኘት) ሪፖርት ለማድረግ፣ በሚከተለው ይደውሉ
፡- 240-777-3000
የአዋቂ ሰዎች የመከላከያ አገልግሎቶች (Adult Protective Services)፣ የጤና እና የሰው ኃይል አገልግሎቶች መምሪያ

የወሲብ በደል/ጥቃት ከተጠረጠረ፣ እንዲሁም ርእሰመምህሩ/ሯ ተቆጣጣሪው/ዋ ወደሚከተለው ቁጥር ይደውላል/ትደውላለች:-
240-773-5400
ልዩ የተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል (Special Victims Investigations Division) ፣ Montgomery County ፖሊስ መምሪያ

4. የጽሁፍ ሪፖርት ለ CPS ወይም APS፣ የጤና እና የሰው ኃይል አገልግሎቶች መምሪያ በ 48 ሰአታት ውስጥ መቅረብ አለበት። የ MCPS ን ቅጽ 335-44 የተጠረጠረን በደል እና ቸልታ/ተገቢ እንክብካቤ ያለማግኘት ሁኔታ ሪፖርት ስማደረግ/ስለማመልከት (Report of Suspected Abuse and Neglect) ይጠቀሙ። አድራሻ እና የስርጭት አካሄዶች በቅጹ ላይ ተመልክተዋል። ይህን መስፈረት በተመለከተ ምንም የተለየ አስተያየት አይደረግም።
5. ሁሉም ሪፖርቶች በልሙጥ (ሌጣ) ፖስታ፣ ታሽገው፣ አድራሻ ተጽፎባቸው፣ እና ምስጢራዊ የሚል ምልክት ተደርጎባቸው መላክ ይኖርባቸዋል። ለት/ቤት እርዳታ/እገዛ እና ማሻሻል (Office of School Support and Improvement) ጽ/ቤት የተላኩ ሪፖርቶችን የያዙ ፖስታዎች በተለመደው ከጽ/ቤት ወደ ጽ/ቤት መላኪያ ፓስታ መደረግ ይኖርባቸዋል።
6. በ Maryland ህግ፣ ማንም ሰው በቀና መንፈስ በደል ወይም ቸል መባልን (ተገቢውን እንክብካቤ አለማግኘትን) ሪፖርት ካደረገ/ች ወይም በማድረግ ከተሳተፈ/ች ወይም በምርመራ ወይም ከዛ ተከትሎ በመጣ የፍርድ ሂደት ከተሳተፈ/ች በሌላ ሁኔታ የበደልን ወይም ቸል መባልን፣ ወይም በምርመራ ወይም ከዛ ተከትሎ በመጣ የፍርድ ሂደት በመሳተፍ ሊመጣ ከሚችል ከሲቭል ተጠያቂነት ወይም ከወንጀል ቅጣት ነጻ ይሆናል/ትሆናለች።
7. ማንኛውም የ MCPS ሠራተኞች፣ የሥራ ተቋራጮች፣ ወይም የበጎ ፈቃድ ሰራተኞች፣ ለ MCPS በሙያዊ ወይም አገልግሎት በመስጠት የስራ ድርሻቸው በቀረቡበት/በተገኙበት ሁኔታ የልጅ በደል እና/ወይም ቸል መባልን ጠርጥረው/ገምተው እና እያውቁ ጉዳዩን ሪፖርት ካላደረጉ፣ ወይም ሆን ብለው ሪፖርት እንዳይደረግ ከከለከሉ ወይም ጣልቃ ከገቡ፣ በጽ/ቤት የማይገባ ጠባይ በማሳዬት እንደ አግባብነቱ እስከ ከስራ መታገድ፣ የኮንትራት አገልግሎቶቻቸው መቋረጥ፣ ወይም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የመስጠት እድላቸው/ጥቅማቸው መቋረጥ የሚያደርሰ እና የሚያጠቃልል የስነ ስርአት ርምጃ ይወሰድባቸዋል። በተጨማሪ፣ በ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ ወይም በሌላ የፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ሰጭ ቦርድ ሥልጣን የተሰጠ ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ፣ በ Maryland ህግ በተቀመጠው መስፈረት/መለኪያ መሰረት፣ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል።

ምስጢራዊ መረጃ የያዙ የተጠረጠረ የበደል እና ችላ የመባል ሪፖርቶች ካልተፈቀደ በቀር ሊሰራጩ፣ ሊበተኑ፣ ወይም ሊገለበጡ/ኮፒ ሊደረጉ አይችሉም።
መግለጽ/ጥ፣ መገልበጥ/ኮፒ ማድረግ፣ ማሰራጨት፣ ወይም በዚህ መረጃ ይዘቶች ላይ መሰረት በማድረግ ማናቸውንም እርምጃ መውሰድ በጥብቅ የተከለከለ ነው።